# ተበላህ ወገኔ አትነሳም ወይ?!!

ማን አድርጎት ያውቃል በየተኛው ሀገር፣
ቤተ - መንግሥት ሆኖ ከታላቁ ወንበር፣
ሀገሩን ለጠላት ወስዶ እሚቸረችር?
እስኪ ሰው ጥሩልኝ መጽሐፉ ይገለጥ፣
ታሪክ አገላብጡ ከውጭ ሆነ ከውስጥ፣
እኔ የማላውቀው እንዲያው ካለ በእርግጥ፣
ሕዝብና ሀገሩን አምርሮ እሚጠላ፣
ለሀገሩ ቀርቶ ለጠላት ያደላ፣
መሪ ከተገኜ ከመለሰ ሌላ::

ብዙ አምባገነኖች በዓለም ላይ ቢኖሩም፣
ባገሩ ላይ ቆሞ ለጠላት የሚቆም፣
ከዕናት ሀገር ይልቅ ጠላት የሚያስቀድም፣
ታሪክ የዘገበው እስከአሁን በዓለም፣
ከኛው ጉድ በስተቀር አንድም ሰው አልታየም::
ተናግሬ ነበር ትናንት ቀደም ብዬ፣
መለስ ጠላት እንጅ መሪ አይደለም ብዬ::

ኢትዮጵያ ሀገሬ እግዚአብሔር ረግሞሽ፣
አዳኝሽን ገድሎ ገዳይሽን ሾመብሽ፣
ባክሊሉ መንበር ላይ መለስን ተካብሽ::
አክሊሉ ሀብተወልድ ታላቁ ዲፕሎማት፣
እባክህ ይቅር በለን እላይ ባለህበት፣
ያገር ነቀረሳዎች ባንተ የተተኩት፣
የለፋህባትን ኢትዮጵያን ሲያጠፏት፣
ባንድ ላይ አልቆምንም ለማዳን ከጥፋት::

ስህተቱ የእኛ እንጅ እነርሱ ምን ያርጉን፣
ከእባብ እንቁላል እርግብ የጠበቅን::
ከአያት ከቅድመ አያት በደም ያገኙትን፣
ከራስ አገር ይልቅ ለጠላት መቆምን፣
ለጠላት ተቀጥሮ አገርን ማጥፋትን፣
በጎሣ መሸንሸን አገር መቸርቸሩን፣
እንዴት ይተውታል ዓላማዬ ብለው የተነሱበትን::

ደምን ከመታለብ ውስጥን ከመቦርቦር፣
እያደር ከመክሣት ከመመንመን በቀር፣
ድሮስ ከአስካሪስ ልጅ ምን እንጠብቅ ነበር?

ባንዳ የባንዳ ልጅ ምሎ ተማምሎ፣
የዘሬን ከምተው ያንዘርዝረኝ ብሎ፣
ሀገር ሲቸረችር ወገን አፈናቅሎ፣
ያርበኛው ልጅ የታል ሀገርን ያቆየው ባጥንቱ ከልሎ?

መከነ ወይ ጎጃም፣ መከነ ወይ ጎንደር፣
መከነ ወይ ሸዋ፣ መከነ ወለጋ የነጆቴ አገር፣
መከነ ወይ ወሎ፣ መከነ ወይ ትግራይ የነአሉላ ሀገር፣
ሀገር በባንዳ ልጅ ተቸርችራ ስታልቅ ውስጧ ሲመዘበር::

ባንዳው ዘሩን ቆጥሮ:- ከደሙ አጣቅሶ፣
ከባንዳ አያቶቹ ቂም አርግዞ ወርሶ፣
ሀገር ሲቸረችር ሲሰጥ ድንበር ቆርሶ፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

እኛስ ጉደኞቹ ያርበኛ ልጆች ባይ፣
የትናንቱ ጀግኖች ያብራካቸው ክፋይ፣
ሀገር ስትጣራ አይሰማንም ወይ፣
የወገንህ ቁስል አይታይህም ወይ?
ፈጽሞ አልገባኝም የእኛ ዝምታችን፣
ከዓይናችን ላይ ስትፈርስ እናት ሀገራችን፡፡
ምን እስክንሆን ነው ከቶ እምንጠብቀው፣
ያላረገን አለ? እስኪ ምኑ ቀረው?

ባንዳ የባንዳ ልጅ በላይህ ላይ ነግሦ፣
ሀገርህን ሲሸጥ እንደ ዳቦ ቆርሶ፣
እህት ወንድምህን አፈናቅሎ አፍልሶ፣
ወገንህ ሲነግርህ ስቅስቅ ብሎ አልቅሶ፣
ልትሰማ ያልፈቀድክ የወገንክን ለቅሶ፣
አረ ማነህ አንተ እስኪ ልጠይቅህ፣

ሰው? የሰው ልጅ?

ወይስ የእንግዴ ልጅ?

ድንገት በስህተት ልጅየው ተቀብሮ አንተ እዚህ የቀረህ?

አሉላ አባ ነጋ የአርበኞች ጎምቱ፣
የተወለድክበት ባድማህ አርጅቶ፣
ጉርጥ ምናምኑን ፍልፈል ጃርት አፍርቶ፣
ሀገርክን አጠፋት ለጠላት አድልቶ፡፡

የዮሐንስ አንገት የተሰየፈብሽ፣
ሰማዕቱ ንጉሥ በደሙ የዋጀሽ፣
የታሪክ ምፀቱ ባንች የደረሰብሽ፣
እርሪ በይ መተማ ጬሂ አፍ አውጥተሽ፣
የዮሐንስ ልጆች ለድርቡሽ ሲሸጡሽ፡፡
ይሄ ያስካሪስ ልጅ በታሪኩ እሚያፍር፣
እሩቅ ቦታ ሳይሄድ ወንዝ ሳይሻገር፣
ማዎቅ ከፈለገ ታሪክን ለመማር፣
የኢትዮጵያ ግዛት የት የት እንደነበር፣
ኢዛና ሃውልት ላይ አለለት በዝርዝር፡፡
የኢትዮጵያ ድንበር ሳይሆን ነብስ ገቢያ ወይም ኦማሐጀር፣
ሃውልቱ ላይ ይየው ከፈለገ ሊማር፣
በኢዛና ጊዜ ኑቢያም የኛ ነበር፡፡

የስልጣን አባዜ መንሰፍሰፍ ለወንበር፣
ተሸጣ ባለቀች በሌለችን ሀገር፡፡
በድርጅት ዙሪያ መታጠሩን ትተህ፣
ባንድ ተሰባሰብ እናት ሀገር ብለህ፡፡
ለድርጅት ጎጆው ትደርስበታለህ፣
አሁን ግን የእናትህ ቤቷ ፈረሰልህ፡፡
የሁሉን አዳራሽ ከመፍረስ ካላዳንህ፣
ቶሎ ተሯሩጠህ አሁን ጊዜ እያለህ፣
ለምትፋጅበት ለዚያ ለወንበርህ፣
ኩርማን ቦታ አይኖርም ነገ እንዳይመሽብህ፡፡

በድርጅት ዙሪያ የምትሻኮተው፣
እስኪ ልጠይቅህ መልስ እፈልጋለው፣



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ይህ የሚያቃኘሀን ወንበር ብታገኘው፣
የትኛው ቦታ ላይ ልታስቀምጠው ነው?

በታሪክ ትምህርት ትናንት በተማርነው፣
ሱልጣን ኢብራሒም ነው አሰብን የሸጠው::
ዛሬ በእኛ ጊዜ እኛ በምናውቀው፣
ዳግማዊ ኢብራሒም፣ ሱልጣን መለስ ነው ሑመራን የሸጠው፣
ሹምባሹ መለስ ነው መተማን ለገንዘብ ለድርቡሽ የሸጠው::
ያስካሪሱ ልጅ ነው የቴዲን ባድማ ቋራን የቀወረው፣
ታሪካዊውን ሀገር ኦሜድላን ያስማማው፣
አሶሳን ጋምቤላን በነሲብ ያቀናው::

ልብ በል ወገኔ ባራቱም ማዕዘን በምትገኝበት፣
በሌለ ወንበር ላይ አንተ ስትባላ፣ አንተ ስትራኮት፣
መተኪያ አልባ እናትክን ሸጠልህ ለጠላት::

እንዴት አይገባህም የወያኔ ሤራ፣
ያንተን ቤት አፍርሶ የሱን ቤት ሲሠራ፣
አንተን እያባላ ኦሮሞን ካማራ፣
አኙዋክን ከንቄር፣ ጉጅን ከሲዳማ፣
እንዳልተወለድን ካንድ እናት እማማ፣
አንድ እንዳንሆንበት ከፋፍሎ እያዳማ፣
መሠረቱን ሲንድ ያንድነቱን ማማ::

አንተን እያስራበ እርሱ ጠግቦ ሲያድር፣
ያንተን አደንቁሮ የእርሱን ልጅ ሲያስተምር፣
መቸ ነው እምትነቃው መቸ ነው እምትማር?
መቸ ይሆን ቀኑ በቀቶህ የምታመር?
መቼ ነው እሚገባህ መቼ ነው እምትነቃ፣
ቆርጠህ የምትለው «አይ! ከእንግዲህስ በቃ!!»

ዛሬ ያልተቆጨህ ሀገርክን ሲሸጣት፣
በንዴት ካልወጣህ ድረቡሽ ሲያቃጥላት፣
ይኸው እምላለሁ በራሴው አንደበት፣
ከመሃለ ምላሴ ፀጉር ንቀልበት፣
ምንም እንደማትል ከጭንህ ፈልቅቆ ሚስትህን ቢወስዳት::
የእኛነት መለኪያው የወንድነታችን፣
ካባት የወረስነው ትልቁ ዕሴታችን፣
አንድም ለናት ሀገር ወይም ለሚስታችን፣
ማሳለፍ ነበረ ክቡር ሕይዎታችን::

ጎበዝ! ምንድነው የሆንነው ከቶ ምኑ ነካን?
የግፉ ዳውላ ፍፁም አልከብድ ያለን፣
የወርደቱ ብዛት ያላንገሸገሸን::

በሮቹ አለቁና ቀርቶብን አባያ፣
የመይሣው አገር ቋራ ነብስ ገብያ፣
መታረስ ጀመረ በሥናር አህያ::

የምክንያቱ አጥር ተንኮታኩቶ ፈርሷል፣
የትግል ቀለሙ ፍንትው ብሎ ጠርቷል፣
ባንድ በኩል ጥቁር በሌላው ነጭ ሆኗል፣
ከመሃል ላይ ሆኖ ወዲህ ወዲያ ባዩ ግራጫው አክተሟል::



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

ይህ ፈታኝ ጊዜ ነው ሁሉን የሚፈትን፣
እኔንም አንተንም፣ እሷንም እሱንም ወቅቱ የጠየቀን፣
ያይዲዮሎጅ ሳይሆን አለዚያም የቡድን፣
ጥያቄው ግልፅ ነው፣ አንድም ሀገር መገደል አንድም ሀገር ማዳን::

እሳት ውስጥ ጨምሮ ሲያጋይህ እያየህ፣
የቃጠሎው ክብደት ለአንተው ተሰምቶህ፣
ከዚህ የባሰማ ምን ይመጣ ብለህ፣
ራስክን በራስህ ነፃ ካለወጣህ፣
ማነን ነው እምትጠብቅ ላንተ እንዲደርስልህ?
ከእሳት ውስጥ ገብቶ ከሳት እንዲያወጣህ?

እንግሊዝ ካስማ መች፣ ግብጽ ድንኳን ጣይ፣
ጥልቅ እንደውቅያኖስ ሰፊ አንደሰማይ፣
እጅግ ታላቅ ድግስ በአባይ ምንጭ ላይ፣
ወያኔ አሳላፊ፣ ሱዳን ተቀባይ፣
ከእንግዲህ ምን ቀረህ ምንድነው እምታይ፣
ተበላህ ወገኔ አትነሳም ወይ?

ከአገኘሁ ገበየሁ

ግንቦት 2000 ዓ.ም.



Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com